OFFICE OF ARTS & CULTURE
CITY OF SEATTLE

# የተስፋ ቡድን (Hope Corps) 2025: መሀል ከተማ የሲያትል ማነቃቂያ መመሪያዎች

## የድጋፍ ገንዘብ ስጦታ አጠቃላይ እይታ

የሲያትል የኪነ ጥበብ እና የባህል ቢሮ (ARTS) ግለሰብ አርቲስቶችን፣ የባህል አምራቾችን፣ የጥበብ አስተዳዳሪዎችን፣ የፈጠራ ሰራተኞችን፣ የማህበረሰብ ቡድኖችን፣ እና የኪነጥበብ እና የባህል ድርጅቶችን ለ Hope Corps እንዲያመለክቱ ይጋብዛል። ለአካባቢው የፈጠራ የሰው ሃይል የስራ እድል የሚፈጥሩ እና ለሲያትል መሀል ከተማ ማህበረሰብ በማህበረሰብ-ተኮር ፕሮጀክቶች፣ ዝግጅቶች፣ ትርኢቶች እና ሌሎችም ደህንነት ላይ የሚያበረክቱ ፕሮጀክቶችን በማቅረብ ማመልከት ይችላሉ።

Hope Corps ለህዝብ ከሚጠቅሙ የስራ እድሎች ከተገቢው በታች እና ስራ አጥ አርቲስቶችን እና የፈጠራ ሰራተኞችን ለማገናኘት ይፈልጋል። የ2025 የ Hope Corps ፕሮግራም **የከንቲባ ብሩስ ሃረል (Bruce Harrell's) መሀል ከተማ ገቢር ማንቂያ እቅድ አካል ነው**፣ እና የገንዘብ ድጋፍ በሲያትል መሃል ከተማ ሰፈሮች ውስጥ በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች የፈጠራ ሰራተኞችን ለሚቀጥሩ ፕሮጀክቶች ይሆናል።

1) ቤልታውን (Belltown)
2) ቻይናታውን - ዓለም አቀፍ ወረዳ
3) ማዕከላዊ መሃል ከተማ
4) ዴኒ ትሪያንግል (Denny Triangle)
5) ፓዮኒር አደባባይ (Pioneer Square)
6) ስታዲየም ወረዳ

ለውሳኔ የቀረቡ ፕሮጀክቶች በ2025 በመንገድ ደረጃ፣ ተደራሽ፣ ውጪ ወይም በሌላ መልኩ በይፋ በሚታዩ ቦታዎች ለህዝብ አሳታፊ ልምዶችን የሚሰጡ እና ታዳሚዎችን ወደ መሃል ከተማ የሚያመጡ ልዩ ዝግጅቶች ወይም እንቅስቃሴዎች መሆን አለባቸው።

ለፈጠራ ሰራተኛ ደመወዞች እና የፕሮጀክት ወጪዎችን ለመደገፍ የገንዘብ ድጋፍ ስጦታዎች ከ**$5,000 - 50,000** ዶላር ድረስ ይደርሳሉ።

**ለመረጃ እና ለማመልከቻ፣ ለብቃት ወይም የመስመር ላይ የቴክኒክ ድጋፍ እና እርዳታ** ለማግኘት የ Hope Corps ፕሮግራም አስተዳዳሪ፣ አሌክስ ሮዝ (Alex Rose) ን በ 206-459-6517 ወይም alex.rose@seattle.gov ያግኙ።

**የአሜሪካ የምልክት ቋንቋን (በቪዲዮ በኩል) ጨምሮ በእርስዎ ቋንቋ ሊያናግሩዎት የሚችሉ አስተርጓሚዎች አሉን።** ብቻ ይደውሉልን እና እርስዎ የሚናገሩትን ቋንቋ ይንገሩን። አስተርጓሚ ስናፈላልግ ጥሪውን እስከሚቀላቀለን ለአጭር ጊዜ እንደሚያስጠብቅዎት ከወዲሁ ይወቁ።

## ማመልከቻ

በ Submittable በኩል በመስመር ላይ ያመልክቱ: https://seattlearts.submittable.com/submit።

የኮምፒውተር ወይም የኢንተርኔት አገልግሎት ከሌልዎት ወይም አማራጭ የማመልከቻ መንገዶችን ለመወያየት ከፈለጉ በተቻለ ፍጥነት የ Hope Corps ፕሮግራም አስተዳዳሪን ያግኙ፣ አሌክስ ሮዝን: alex.rose@seattle.gov.

## የማብቂያ ዕለተ ቀን

**ማክሰኞ፣ መስከረም 3 ቀን 2024፣ ከምሽቱ 5:00 ሰአት ፓሲፊክ**

*ማመልከቻዎን ለማጠናቀቅ እባክዎ በቂ ጊዜ ይስጡት። ከማብቂያ ዕለተ ቀን ከምሽቱ 5 ሰዓት (ፓሲፊክ) በኋላ የቀረቡ ማመልከቻዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።*

## ብቁነት

**እርስዎ እና ለውሳኔ ያቀረቡት ፕሮጀክት የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ከሆነ** ለ Hope Corps የገንዘብ ድጋፍ **ለማመልከት ብቁ ነዎት**:

- እርስዎ ሲያትል አካባቢ ውስጥ የሚገኙ/ የሚቀመጡ ግለሰብ አርቲስት፣ ድርጅት፣ ወይም በማህበረሰብ ላይ የተመሰረተ ቡድን፣ ወይም ሲያትል በመደበኛነት ሥራ የሚያቀርቡ ከሆኑ።
  - ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው፣ አካል ጉዳተኛ ሰዎች፣ አዲስ ሰፋሪዎች እና የስደተኛ ማህበረሰቦች፣ እና የቀለም ማህበረሰቦችን ጨምሮ በስርዓታዊ ጭቆና እጅግ የተጎዱ ማህበረሰቦችን የሚወክሉ ድርጅቶች እና አርቲስት ግለሰቦች እንዲያመለክቱ ይበረታታሉ።
- የእርስዎ ፕሮጀክት በጥር 2025 እና በታህሳስ 2025 መካከል መከሰት አለበት።
- የእርስዎ ፕሮጀክት እና ተዛማጅ የህዝብ ጥቅማጥቅሞች በተገለፀው የመሀል ከተማ ገቢር ማንቂያ እቅድ ገደብ ውስጥ በመሀል ከተማ ሲያትል ውስጥ መከናወን አለባቸው:
  - ቤልታውን (Belltown)
  - ቻይናታውን - ዓለም አቀፍ ወረዳ
  - ማዕከላዊ መሃል ከተማ
  - ዴኒ ትሪያንግል (Denny Triangle)
  - ፓዮኒር አደባባይ (Pioneer Square)
  - ስታዲየም ወረዳ
- የእርስዎ ፕሮጀክት ከሶስቱ የትኩረት ምድቦች አንዱን ወይም ከዛ በላይ ማስተናገድ አለበት።
- የእርስዎ ፕሮጀክት ሕዝቡ እንዲሳተፍ ማስተዋወቅ እና ለሰፊው ህዝብ – የሲያትል ነዋሪዎች፣ ሰራተኞች እና ጎብኚዎች – ተደራሽ መሆን አለበት። ይህ በዋናነት ከእንግሊዝኛ ሌላ ቋንቋ ለሚናገሩ ሰዎች እና አካል ጉዳተኞች በነፃ በዝግጅቶቹ የመገኘት አማራጭ እና ተደራሽነትን ያካትታል። ዝግጅትዎን የበለጠ ተደራሽ ለማድረግ እርዳታን መጠቀም የሚችሉ ከሆነ እባክዎ alex.rose@seattle.gov ያግኙ።
- የእርስዎ ፕሮጀክት በደመወዝ፣ በትምህርት ደመወዝ፣ ወይም በኮንትራት ክፍያዎች ቢሆን ለእያንዳንዱ የፈጠራ ሠራተኛ* ክፍያ መክፈል አለበት። የመኖሪያ ክፍያ ስንል በሰዓት $32 ዶላር ወይም ከዚያ በላይ ብለን እንገልፃለን (ይህ ለወጣቶች እና ተማሪዎች ሊለይ ይችላል)።
- የእርስዎ ፕሮጀክት ምናባዊ አካል ሊኖረው ይችላል፣ ነገር ግን በዋናነት በአካል በመገኘት የሚቀሰም ልምድ መሆን አለበት።
- የእርስዎ ፕሮጀክት ጊዜያዊ የጥበብ ተከላ ከሆነ ቢያንስ ለ 3 ወራት መታየት አለበት።

***የፈጠራ ሰራተኞች** አርቲስቶችን፣ የፈጠራ ሥራዎች አመንጪዎችን፣ የባህል ሰራተኞች እና በእነዚህ መካከል ያሉ ሁሉንም ያካትታሉ።

## የድጋፍ ገንዘብ

የገንዘብ ድጋፍ መጠን ከ **$5,000 - $ 50,000 ዶላር መጠን ይደርሳል።**

የሽልማት ገንዘቡን ለአርቲስት ክፍያዎች፣ የግብይት እና የማስተዋወቂያ ክፍያዎች፣ የፕሮጀክት አስተዳደር እና የሰው ሃይል ወጪዎች፣ የዕቃ አቅርቦቶች፣ የመሳሪያ ኪራዮች ወይም ሌሎች ከምርት ጋር የተዛመዱ ወጪዎች፣ ለሚፈለገው ኢንሹራንስ እና ከ10% በላይ ያልሆኑ ለምግብ ነክ ወጪዎች ሊጠቀሙበት ይችላሉ። ምናልባት በድጋፍ ገንዘብ ስጦታ የፕሮጀክት ሥራ አስኪያጁ ተጨማሪ ወጪዎች በቅድሚያ ተፈቅዶ ሊጸድቁ ይችላሉ።

## የመረጃ አውደ ጥናቶች

ስለዚህ የገንዘብ ስጦታ እና የእርስዎን ከሁሉ ምርጥ የሆነ ማመልከቻ እንዴት ማስገባት እንደሚችሉ የበለጠ ይወቁ።

**አውደ ጥናት 1 (ምናባዊ)**
ማክሰኞ፣ ሀምሌ 30 ቀን 2024፣ ከጥዋቱ 10:00 - 11:00 ድረስ።
[የበአክብሮት መልስ አገናኝ]

**አውደ ጥናት 2 (በPioneer አደባባይ በአካል በመገኘት)**
ሰኞ፣ ነሐሴ 5 ቀን 2024፣ ከምሽቱ 6:00 - 7:30 ሰዓት ድረስ።
[የበአክብሮት መልስ አገናኝ]

**ወርክሾፕ 3 (ምናባዊ)**
ሐሙስ፣ ነሐሴ 15፣ ከጥዋቱ 11፡30 - ከሰዓት 12፡30 ድረስ።
[የበአክብሮት መልስ አገናኝ]

**ወርክሾፕ 4 (ቤልታውን ውስጥ በአካል በመገኘት)**
ቅዳሜ፣ ነሐሴ 17፣ ከጥዋቱ 11፡00 - ከሰዓት 12፡30 ድረስ።
[የበአክብሮት መልስ አገናኝ]